# <u>የአዲስ ነገር አዘጋጆችና</u>
# <u>ስደት ለምን?</u>

በቅርቡ የአዲስ ነገር አዘጋጆች በላኩት መግለጫ አማካኝነት አገር ጥለው መኮብለላቸው ተሰምቷል፡፡ ይህን ተከትሎም ጉዳዩ የሳምንቱ የኢትዮጵያ cyber፣ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ ቆይቷል፣፡ እኔ በግሌ የጋዜጣዋ የዘወትር አንባቢ ነበርኩ፡፡ እናም በዚህ ምክንያት የጋዜጣዋን ሁለንተናዊ ይዘት የማወቅ እድል ስለነበረኝ በጉዳዩ ላይ የበኩሌን ለማለት ፈለኩና የሚከተለውን ጽሑፍ ፃፍኩ፡፡ ጽሑፉ ሁለት ዋነኛ ክፍሎች ይኖሩታል - የጋዜጣዋ አዘጋጆች ለምን እንደተሰደዱ የራሴን ምክንያታዊ ግምት የምተነትንበት ክፍልና አዘጋጆቹ በመግለጫቸው ለስደት ዳርጉናል ያሉት ምክንያት ተገቢ አለመሆኑን የማሳይ ሌላ ክፍል

## 1. የአዲስ ነገሮች ስደትና ምክንያቱ

አዲስ ነገሮች የአገሪቱን የሚዲያ ኢንዱስትሪ ከተቀላቀሉ ከ2 ዓመት ብዙም አይበልጥም፡፡ ይሁንና በዚህ አጭር ጊዜ ወስጥ ለአገሪቱ የሚዲያ ኢንዲስትሪ አሉታዊና አዎንታዊ አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡ ከአዎንታዊ አስተዋጽኦ ዋናው የቋንቋ ጥራት ነው፡፡ የአዲስ ነገር ፀሃፊዎች በተደጋጋሚ እንዳስተዋልኩት የአማርኛ ቋንቋ በደንብ አድርገው የሚያውቁ ናቸው፡፡ ሌሎቹ በአገሪቱ የሚገኙ ጋዜጦች ከዚህ የጋዜጣዋ ጠንካራ ጐን ትምህርት እንደሚቀስሙ ተስፋ አደርጋለሁ፣፡ ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ጋዜጣዋ ብዙ አሉታዊ ጐኖች አሏት፡፡ በዚህ የአጭር ጊዜ ቆይታዋ ጋዜጣዋ በጋዜጠኝነት ሙያ ወስጥ የpostulate ደረጃን የተቀዳጁ አለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያላቸውን የሙያ ስነ ምግባር ምርሆዎችን አልቀበልም ማለቷ ሳያንስ ለተለያዩ እኩይ ሃሳቦች ማስተጋቢያ መንገድ እንድትሆን አዘጋጆቹ ፈቅደዋል፡፡ በእኔ እምነት አዘጋጆቹ ደፍረው ሚናገር ያልፈለጉት ይህ ሰህተት ነው ታዲያ ለስደታቸው ምክንያት ሆኖ የሚታየኝ፡፡ በሚከተለው ሜልኩም ስደታቸውና የጋዜጣቸው ድክመት እንዴት እንደሚገናኝ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

### 1.1. የጭር ሰል አልወድም ፖለቲካ

የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ጊዜ ቃል የተገባለትን ነገር የተከዳ ህዝብ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ምንም እንኳን ቁጥራቸው ቀላል የሚይባል በዚህች አገር የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተደራጀ ፖለቲካን በአደባባይ ማካሄድ በፈልጉም ለብዙ ዘመናት የኢትዮጵያ

ፖለቲካ ወስጥ የሚይታሰብ እና የሚይታለም ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህ የታሪክ አጣበቂኝ መካከል ነው ታዲያ የ1983 አብዮት ምስጋና ይግባው እና በኢትዮጵያ ወስጥ የተደራጀን ፖለቲካ ማካሄድ ህገ – መንግስታዊ ዋስትና እና መንግስታዊ ይሁንታን የተቀዳጀው፡፡ ይሁን እና በተፈጥሮው የሰው ልጅ ለዘመናት የተከለከለወን ነገር ሲያገኘው ጉዳዩን እንዴት ማጠቀም እንዳለበት ከአለማገንዘቡ የተነሳ የተሰጠወን መብት አላግባብ እና ህግን በማይላለፍ አኳኋን ሲጠቀምበት ይስተዋላል፡፡

በኢትዮጵያ የማገኙ የዚህ መብት ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችም ይህንን የሰው ልጅ መሠረታዊ ወስኑነት በማጋራት በህገ መንግስቱ ያኘወን የመደራጀት መብት ላልታለማለት አላማ ፣ ጠብብ ቡድናዊ ፍላጐት እና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች መብትን በሚጋፋ ሜልኩ ሲጠቀማበት ተስተወሏል፡፡

ነገር ግን የዲሞክራሲ ስርዓቱ ተዋናዮቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያዳበሩ ከማጡት ልምድና ክህሎት የተነሣ ፖለቲካችን እና ፖለቲከኞቻችን ወደ አጠቃላይ ስክነት በማምራት ላይ ይገኛሉ፡፡ እንደአለመታደል ሆኖ ስክነትን የሚጠሉ እና የሞትን ያህል የሚፈሩ የተቃወሞ ፖለቲካ ወገኖች አልጠፉም፡፡ ጨልማ የራሱ የሆነ ህልወነት የሌለው እና ብርሃን በሌለበት ቦታ ብቻ እንደማገኘው ሁሉ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ህይወት ወስጥ ህልወናቸወን የሚያረጋግጠብት ብቸኛ መንገድ ሁከትና ብጥብጥ እንደሆነ የሚከማቸው የፖለቲካ ኃይሎች በሚፈጠራቸው ስክነቱ የተሟላ አልሆነም፡፡

በአጀንዳ ድርቅ እና በተሟጭ በፖለቲካ ፕሮግራም እጦት የተመቱት እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች የኢትዮጵያ የፖለቲካ ስክነት አንደኛ ጠላታቸው ነው፡፡

ይህ የሚሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሲሰክን ህዝቡ በረጋ መንፈስ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያቀርቡትን አሟጭ የሚመዛዘን አቅም ስለሚኖረው ባዶነታቸወን ስለሚረዳ የፖለቲካ ህልወናቸው እንደሚያከትም ስለሚረዱ ነው፡፡ ይህ ስክነት የአስፈራቸው የፖለቲካ ኃይሎች የኢትዮጵያ ፖለቲካን ወደ ሁከት እና ግርግር የሚመሩ አንዳች ምድራዊ ኃይል እንዲፈጠር ፀሎት ሲያደርጉ በነበሩበት ጊዜ ነው ታዲያ አዲስ ነገር የደረሰላቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ነው ታዲያ አዲስ ነገሮች ከተቃዋሚዎች ጋር ባላቸው ምክንያታዊ እና ስሜታዊ ቁርኝት ከኢትዮጵያ በሚፈርጠጥ የስክነት ፖለቲካን በሚደናቀፍ ለተቃዋሚዎች ያላቸወን አጋርነት ዳግም ለሚያጋገጥ የተስማሙት እናም አደረጉት ፍቅር እወር ነው አይደል የሚባለው፡፡

## 1.2. የአዲስ ነገሮች ፖለቲከኝነት

አዲስ ነገር ወስጥ በጋዜጠኝነት ይሣተፉ የነበሩት አብዛኞቹ ግለሰቦች ፍፁም ፖለቲከኞች ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ከተደራጀ ፖለቲካ ከ1997 ዓ.ም. ምርጫ በኋላ በተቃዋሚዎች ጐራ በደረሰው ሜፈረካከስ ተስፋ ቆርጠው ጋዜጠኝነትን የፖለቲካ አላማዎቻቸው እንደማስከፈፀሚያ ለማጠቀም የፈለጉ ግለሰቦች ነበሩ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የጋዜጠኝነት ካባን በማጥለቅ ህብረተሰቡ ለነፃ ጋዜጠኞች የሚሰጠውን አሜኔታ እና ከበሬታ እንዲሁም ሞራላዊ ሜልህቅ እና ከማሳል ሞያ ከተሰሜሩ ጋዜጠኞች አና የመብት ተሜጋቾች <<sense of solitarily>> ለማግኘት በአለመ ሜልኩ የተሰላ የፖለቲካ ሂሣብን መሠረት በሜድረግ ጋዜጠኝነትን የተቀላቀሉ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ታዲያ እያደር የእነዚህ ግለሰቦች ማንነት ህብረተሰቡ እየተረዳ ሲመጣ እና እነርሱም ለተቃወሞ ፖለቲካ ያላቸው ወገንተኝነት “over mind” ሆኖባቸው ከአደባባይ በስተጀርባ የተሰሉትን የፖለቲካ ሃሳቦች ገሸሽ በሜድረግ የተቃወሞው ወገን ሹፌሮች መሆን ሲጀምሩ ህብረተተሰቡ በተሳሳተ ሜልኩ የቸራቸው የተአሜኒነት እና የሜዝናዊነት ልኬትን ነፈጋቸው፡፡ በዚች አገር ወስጥ መኖር የሜፈልጉት ብቸኛው ምክንያት ጋዜጠኛ ማስለው አገሪቱ የተያያዘችውን የሰላሜዊና ዴሞክራሲያዊ ጉዞ ሜስናከል ስለነበር ህዝቡ ይህን ድብቅ አላማቸውን እየተረዳ በማምጣቱ በአገሪቱ ለመኖራቸው ብቸኛ ምክንያት የነበረው ጉዳይ ማሣካት ስለተሣናቸው አገሪቷን ጥለው ኮበለሉ፡፡

## 1.3. የቀለም አብዮተኞች ስንክሳር

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለሜደ የመጣው ነገር በኢኮኖሚ እና ወታደራዊ ኃይላቸው የበላይ ነን የሚሉ ኃይሎች በሌሎች አገሮች ላይ የሜያዙትን ያልተገባ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ለወጥ የሜይቀበሉ አገሮችን ለማንበርከክ ያለመ የቀለም አብዮት ስንክሣር ወደአለሜችን ፖለቲካ ብቅ ብሏል፡፡ ይህ ስንክሣር ከበስተጀርባው ያሉ ኃይሎች የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ኃያልነት የተነሣ ፈርጀ ብዙ አካላትን የሜያሣትፍ እና ወስብስብ የሆኑ ታክቲኮችን ጥቅም ላይ የሜያወል እንቀስቃሴ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም ተጠያቂነቱን እና የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግቦችን ከእነዚህ ያልተገባ ተጽእኖ የሜያሣድሩ ኃይሎች አሻፈረኝ በሜለት ከሰፊው ህዝብ ጥቅም አንፃር በመቃኘቱ የቀለም አብዮተኞች ኢላማ ሆኗል፡፡

የቀለም አብዮት በባህሪው ደግሞ ጋዜጠኝነትን ለዚህ ርካሽ አላማ ለማዋል ይቋምጣል፡፡ አዲስ ነገሮችም የቀለም አብዮት ያቀረበላቸውን የሁከትና የብጥብጥ ፊሽካ የመንፋት ግብዣ በሙሉ ልብ በመቀበል ራሳቸውን ከኢትዮጵያ የሚዲያ ኢንዱስትሪ በማገለል ወደ አሜሪካ ፈርጥጠዋል ፡፡

በብዙዎች ዘንድ ለቀለም አብዮት የመንፈስ አባትና የኢኮኖሚ ደጀን እንደሆነ ተደርጐ የሚቆጠረው የኢትዮጵያ ዲያስፖራ በዚህ ሰዓት እና ወቅት አንድም በኢኮኖሚ ቀውሱ ምክንያት ሁለትም በ1997 ዓ.ም. ምርጫ የተከተለውን ስልት ኢ-ትክክለኛነት በሚዳት እራሱን ከንቁ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አቅቧል፡፡

አዲስ ነገሮች ታዲያ በስደታቸው የተዳከመውን የዲያስፖራ እንቅስቃሴ ህይወት ለመዝራት እና ለቀለም አብዮቱ የኢኮኖሚ ደጀን ሆኖ እንዲያገለግል የታሰበውን ዲያስፖራ የሚዲያ ወጠቶችን በዚያው ዲያስፖራዉ በሚኙበት ለማብርከት በማሰብ የአሜሪካ ከተሞችን ከኢትዮጵያወያን ከተሞች በላይ መርጠዋል፡፡

## 2. የአዲስ ነገር አዘጋጆች ስደትና በመገለጫው የተነሱ ምክንያቶች

የአዲስ ነገር አዘጋጆች ከወደ ዋሽግተን የላኩት መግለጫ እንደሚያሳየው ለስደታቸው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የደህንነት ተቋማት ወከባ፣ በፀረ ሽብርተኝንት ህጉ ለመክሰስ በመንግስት እየተደረገ ያለው ዝግጅት ወዘተ ናቸው፡፡  በአጠቃላይ የዚህ መግለጫ ይዘት ገዥው ፓርቲ ለሚዲያ የነፃነት ያለውን ቁርጠኝነት ጥርጣሬ ወስጥ ለማከተት ባለመ ሁኔታ የተጠናቀሩ ሰንካላ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ጉዳዩ የሚዲያ ነፃነት ስለሆነና ይህም ደግሞ የሁሉም የኢትዮጵያ ዜጐች ጉዳይ እስከሆነ ድረስ እኔም በሁለት ሜሉኩ የሚከተሉን ትንታኔ አቀርባለሁ፡፡ የደህንነት ተቋማት በእወነት የአዲስ ነገር ጋዜጦችን ያዋክቡ ነበር? የፀረ ሽብርተኝነት ህጉስ በአዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ ጥቅም ላይ ሊወል ይችላል? በእርግጥ ገዡው ፓርቲስ ለሚዲያ ነፃነት ያለው ቁርጠኝነት አጠራጣሪ ነውንስ?

### 2.1. የደህንነት ተቋማት

የኃላ ታሪካችንን የሚያወቅ ማንም ሰው እንደሚረዳው በአገራችን የደህንነት ተቋማት ባለፉት ስርዓት ስማቸው እንደሚያሳየው የኢትዮጵያን ህዝብ ደህንነት ለማጠበቅ ሳይሆን ደህንነትቱን ለሜጊን ጥቅም ላይ ወለዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ህዝቡ ደህንነት የሚለው ቃል በትክክለኛ የአማርኛ ፍቺው መረዳትን አቁሞ ከችግርና እስራት ጋር አያይዞት

ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ታሪካዊ ስህተት ሊታናና ሊታረም ግድ ሆነና የደህንነት ተቋማት ትክክለኛ በሆነው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የህዝብ ደህንነት በማጠበቅ ተልእኮ ከተሰሚ እነሆ 19 ዓመት አለፈው፡፡ ለ1982 አብዮት ምስጋና ይግባውና በኢትዮጵያ ህዝቦች የእለት ተእለት ህይወት ወስጥ ጫልቃ ለመግባት የሚዋከረው የደህንነት ተቋም ዓላማውና ተልእኮው እንዲሁም የየእለት እንቅስቅሰው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ከጥቃት መከላከል ብቸኛ ግቡ በሆነው የደህንነት ተቋም ተተክቷል፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ነው ታዲያ አዲስ ነገሮች የደህንነት ተቋማት ወከባ ስለባ ሆነናል ብለው መግለጫ ያወጡት፡፡ ይህ መግለጫ ሲጀመር ሃቅ ኖሮት ሳይሆን ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ህዝብ ለደህንነት ተቋማት ያለው ጥላሸት የተቀባ ስእል በመቀርኮር የህዝቡን ሃዘኔታ ለማግኘት የሰላ የፖለቲካ መላ ነው፡፡ ነገር ግን እዚህ ጋር ሊጠይ የሚገባው ጉዳይ የኢትዮጵያ ህዝብ ለደህንነት ተቋማት ያለው የተዛባ አረዳድ እንዲቀየር የሚያደርግ በተግባር የታገዘ በቂ ጊዜ (19 ዓመታት) ማግኘቱን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ላለፉት 19 ዓመታት እንደተረዳው የደህንነት ተቋማት ብዙ ጊዜ ከጥቃትና ከሽብርተኝነት አደጋ ጠብቀውታል፡፡ ስለሆነም አዲስ ነገሮች ሜዳ ላይ ያለው ሃቅ ስለቀየረ በደህንነት ተቋማት እንደተዋከባችሁ አድርጋችሁ ያቀረባችሁት መግለጫ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ አንድም የፖለቲካ ትርፍ አያስገኝላችሁም፡፡

## 2.2. ገዥው ፓርቲና የሚዲያ ነፃነት

የአዲስ ነገር አዘጋጆች መግለጫ በአንክሮ ያነበበ ሰው ሚዳት እንደሚችለው የመግለጫቸው ማሻና ሚረሻ ገዥው ፓርቲ የሚዲያ ነፃነት አፋኝ እንደሆነ አድርጎ ማሳል ነው፡፡ እዚህ ላይ ማሳት ያለበት ምክንያታዊ ጥያቄ በእርግጥ ይህ እውነታ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው

በመሰረቱ የሚዲያ ተቋማት አስፈለጊነት የሚመነጨው ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ በሚያበረክቱት መተኪያ የሌለው አስተዋጽኦ ነው፡፡ ስለሆነም ገዥው ፓርቲ የሚዲያ ነፃነትን ያፍናል ማለት በዴሞክራስያዊ ስርዓት አያምንም እንደማለት ነው፡፡ ከዚህ አነፃር ገዥው ፓርቲ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ያለውን ቁርጠኝነት በሚከተለው ሚልኩ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

2.2.1. የታሪክና የሞራል ዳራዎች፡- ህወሓት በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ አስፈላጊነት አጠቃላይ የሆነ የፖለቲካ መግባባት በተፈጠረበት ጊዜ የተመሰረተ ድርጅት ነው፡፡ በተመሳሳይም አሁን አገሪቷን በመምራት ላይ ያሉት የኢህአዴግ ሚዎች ያኔ ወርቅ

የሆነው ወጣትነታቸውን የሰውት ለዚህ ክቡር አላማ ነበር - ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለማንባት፡፡ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ደግሞ ኢህአዴግ በዚህ አላማ ቃል ኪዳን ምክንያት ብዙ ወጣት አባላቱን ያጣ ድርጅት ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ በተጠቀሰት የሞራልና የታሪክ ምክንያቶች ኢህአዴግ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት በተጠቀሰት የሞራልና የታሪክ ምክንያቶች ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያለው ቁርጠኝነት ጥርጣሬ ወስጥ የሚገባ አይደለም፡፡

2.2.2. የፖለቲካ ዳራ፡- ኢትዮጵያ የተለያዩ ፖለቲካዊ ፣ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ አበቃቀል ያላቸው የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ነች፡፡ በዚህም ምክንያት አገሪቱ እንደ አገር መቆየት ካለባትም ሆነ አገሪቷ ወስጥ ትርጉም ያለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ከተፈለገ በቅድሚያ የህዝቡ በጐ ፈቃድ ማግኘትን የግድ ይላል፡፡ ይህን የህዝቡን በጐ ፈቃድ የማገኛ ብቸኛው መንገድ ደግሞ ዴሞክራሲ ነው፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ መቀራዊ አፈጣጠር ዴሞክራሲን የግድ የሚል የፖለቲካ ዳራ እንዲኖር ስለሚያደርግ ኢህአዴግ ዴሞክራሲን በአገሪቷ ወስጥ ተግባራዊ እያደረገ ነው፡፡

2.2.3. የኢኮኖሚ ዳራ፡- ድርጅቱ የጽንሰ ሃሳብ መነሐቻ እንደተቀመጠው የኢህአዴግ የፖለቲካ - ኢኮኖሚ ፕሮግራም የተቃኘው ከዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት ጽንሰ ሃሳብ አኳያ ነው፡፡ ይህ ልዩት ደግሞ ዴሞክራሲና ልማት በእጅጉ የሚቆራኝ ሲሆን ዴሞክራሲ ልክ እንደ ልማት ቅድመ ሁኔታ አድርጐ ነው የሚያስቀምጠው፡፡ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ይህ ሃልዩት ትርጉም ያለው ሆኖ የሚገኘው ደግሞ ኢትዮጵያ ያላት ኃብት ሜሬት የሰው ጉልበት መሆኑ ነው፡፡ የሰወን ጉልበት አጠቃላይ ማንቃቃትን በመፍጠር ለኢኮኖሚያዊ እድገት ለማዋል ደግሞ አገራዊ መግባባትን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ስኬት የሚያበቃው ብቸኛው መንገድ ደግሞ ዲሞክራሲ ነው፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ወስጥ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባት ጠንክሮ እንዲሰራ የሚያደርገው የኢኮኖሚ ፕሮግራም ስላለው ለዲሞክራሲ ያለው ቁርጠኝነት ጥርጣሬ ወስጥ የሚያስገባ ነገር የለም፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀተታ ሚዳት እንደሚቻለው የኢህአዴግ ቁርጠኝነት ለዲሞክራሲ የሚመነጨው ድርጅቱ ካለው ሞራላዊና ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዳራ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ኢህአዴግና ዲሞክራሲ መቀራዊም ሆነ ሰብአዊ በሆነ ምክንያት ላይለያዩ የተያያዙ የሁለት ሣንቲም አንድ ገፅታዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም ኢህአዴግ ለዲሞክራሲ ያለው ቁርጠኝነት ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ እስከሆነ ድረስ ለፕሬስ ነፃነት ያለወን ተቆርቋሪነት በተመሳሳይ ሚሌኩ

የፀናና የሚያሸረሽር ይሆናል። ስለዚህ ኢህአዴግ ለፕሬስ ነፃነት ተቆርቋሪ አይደለም የሚለው ክስ ውሃ የሚያቋጥር ከመሆኑ የባሰ ለፕሮፓጋንዳው አሰራሮች የሚያስገኘው አንዳችም እርባና ያለው የፖለቲካ ትርፍ አይኖረውም።